**ADDA BILISUMMAA OROMOO (ABO-WBO)**

**OROMO LIBERATION FRONT** جبهة تحرير أورومو

**Date**: August 28, 2025 **Nr.**: IEABO WBO/08-04/02-2025

**Guyyaa**: Hagayya 28, 2025 تاريخ **Lakk.**: IEABO-WBO/08-04/02-2025 رقم

# በመንግስት የሚደገፈው "ፋኖ ሚሊሻ" በምስራቅ ወለጋ ሰላማዊ ሰዎች ላይ እያደረሰ ያለውን ጥፋት በተመለከተ

***(የኦነግ-ኦነሠ መግለጫ)***

በኦሮሚያ፣ ምስራቅ ወለጋ ዞን ራሱን "የወለጋ ፋኖ" ብሎ የሚጠራው በመንግስት የሚደገፈው ታጣቂ ቡድን በሰላማዊ ህዝብ ላይ እየፈጸመ ያለው የሃይል እርምጃ መቀጠሉን የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ይገነዘባል። ይህ የጥፋት ቡድን በመጀመሪያ የተደራጀና፣ የታጠቀው በአገዛዙ ሲሆን ከአብይ መንግስት የሚያገኘው የሎጂስቲክስ ድጋፍም ቀጥሎ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስም በአገዛዙ የሚሊሺያ ኃይል ውስጥ መደበኛ በታዎችን ይዞ የነበረና  በአካባቢው ላለው አለመረጋጋት አንዱ መሳሪያ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል።

የዚህ ሚሊሻ ህልውና ያስፈለገበት የገዥው ቡድን ስልታዊ አላማዎች በዋናነት ሁለት ናቸው። እነሱም፡-

1. በአከባቢው ባለው የኦሮሞ ማህበረሰብ ውስጥ የፍርሀት ድባብ እንዲሰፍን በማድረግ በኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት (OLA) በሚመራው ቅቡልነት ባለው የነጻነት እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን ሰፊ ህዝባዊ ድጋፍ እና ተሳትፎን ለማፈን እና፣

2. በህዝቦች መካከል በተለይም በሁለቱ የአገሪቱ ትላልቅ ማህበረሰቦች መካከል ያለውን አብሮነት ለመሸርሸር እና የጎንዮሽ አለመግባባት/ ግጭትን ለመፍጠር የተነደፈ የእርስ በርስ ግጭት እንዲፈጠር እና እንዲቀጥል ማድረግ ነው።

በመሆኑም የዚህ ሚሊሻ ተግባር በህዝባችን ላይ መሰረታዊ የመብት ጥሰቶች እንዲቀጥሉ አድርጓል። ይህንን ወንጀለኛ ቡድን የፈጠረው እና በቀጣይነት ህልውና እንዲኖረው የሚያስችለው ቀዳሚ አካል አገዛዙ በመሆኑ  የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት (OLA) ለእነዚህ እኩይ ተግባራት በቀጥታ አገዛዙን ተጠያቂ ያደርጋል።

ስለዚህ የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት (OLA)፤ ሰላማዊ ህዝብን ከነዚህ በመንግስት የሚዘወሩ/የሚደገፉ የጥፋት ሃይሎች ጥቃቶች ለመጠበቅ ሁሉንም አስፈላጊ እርምጃዎች ለመውሰድ አሻሚ ያልሆነ መብትና ሀላፊነት ያለው መሆኑን ያሳውቃል። በመሆኑም በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የአገዛዙን አጥፊና ከፋፋይ ጥቅም በሚያስጠብቅ ማንኛውንም ቡድን ላይ እርምጃ ለመውሰድ እንገደዳለን። ይህ ታጣቂ ሚሊሻ በመንግስት

የሚደገፍ የሽብር መሳሪያ መሆኑን ሁሉም ኃላፊነት የሚሰማቸው የፖለቲካ ተዋናዮች እና የሲቪክ ድርጅቶችም፣ በዚሁ ልክ እንዲያውቁት ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የኦነግ-ኦነሠ ከፍተኛ ዕዝ
ኦገስት 28 ቀን 2025